https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
አዲስ አበባ መጋቢት ፱ ቀን ፪ሺ፲፬ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No 16
ADDIS ABABA 18th March, 2022

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፰/፪ሺ፲፬
የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ..ገጽ ፲፬ሺ፷

**Content**

Proclamation No. 1268/2022
Private Organization Employees' Pension Proclamation........................................Page 14060

https://chilot.me

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፰/፪ሺ፲፬**

**የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ**

የማኅበራዊ ዋስትናን ሥርዓት በማስፋፋት ደረጃ በደረጃ ለዜጎች እንዲዳረስ ማድረግ ከሀገሪቱ ማሕበራዊ ፖሊሲ አንዱ አካል በመሆኑ፤

የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድን እና ፈንድን በማሻሻልና በማጠናከር ዘላቂነትና አስተማማኝነቱን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

በሀገሪቱ እየታየ ካለው ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት ጋር የተጣጣመና ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋትና አሠራሩን ማዘመን ስለሚገባ፤

የሥርዓቱ መስፋፋትና ተጠናክሮ መቀጠል ለማኅበራዊ ፍትሕ፣ ለኢንዱስትሪ ሰላም፣ ለድህነት ቅነሳና ለልማት ጉልህ አስተዋጽዖ ስለሚኖረው፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**PROCLAMATION NO 1268/2022**

**PRIVATE ORGANIZATION EMPLOYEES' PENSION PROCLAMATION**

**WHEREAS**, it is part of the country's social policy to expand the social security system and reach citizens step by step;

**WHEREAS**, it is found necessary by strengthening and improving private organization employees' pension scheme and pension fund to ensure the reliability and sustainability;

**WHEREAS**, in line with the country rapid economic and social development, the system needs to adapt and update to benefit citizens;

**WHEREAS**, the expansion and consolidation of the system will significantly contribute to social justice, industrial peace, poverty reduction and development;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

የአንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ 80001
Negarit G. P.O.Box 80001

https://chilot.me



## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፰/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "**የግል ድርጅት ሠራተኛ**" ማለት በግል ድርጅት ውስጥ ከአርባ አምስት ቀናት ላላነሠ ጊዜ ደመወዝ እየተከፈለው ለተወሠነ ወይም ላልተወሠነ ጊዜ ወይም የተወሠነ ስራ ለመስራት የተቀጠረ ሠራተኛ ሲሆን የስራ መሪን ይጨምራል፤

፪/ "**የግል ድርጅት**" ማለት ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለእርሻ፣ ለኮንስትራክሽን፣ ለማህበራዊ አገልግሎት ወይም ለሌላ ሕጋዊ ዓላማ የተቋቋመ ሠራተኛ ቀጥሮ ደመወዝ እየከፈለ የሚያሠራ የግል ተቋም ወይም ሰው ሲሆን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን እና ማህበራትን ይጨምራል፤

፫/ "**መንግሥት**" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል መንግሥትን እና የክልል መንግሥታትን ያጠቃልላል፤

፬/ "**ክልል**" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ (፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተቋቋሙትን እና የሚቋቋሙትን ሌሎች ክልሎች እንዲሁም የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

## PART ONE

## GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Private Organization Employees' Pension Proclamation No. 1268/2022".

**2. Definition**

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1./ "**Private organization employee**" means a salaried person employed in a private organization for not less than forty five days for definite or indefinite period of time or piece of work including managerial employees;

2/ "**Private Organization**" means an organization established to engage in commerce, industry , agriculture, construction, social service or in any other lawful activity and which has salaried employees and includes charities and associations;

3/ "**Government**" means the Federal Government and includes the Regional States of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

4/ "**Region**" means any Region referred to in Article 47 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, which includes other Regions established or will be established in accordance with Sub-Article (2) of this Article, as well as the Administrations of Addis Ababa and Dire Dawa;

https://chilot.me



፭/ **"የግል ድርጅት አገልግሎት"** ማለት በግል ድርጅት ሠራተኞች የሚፈጸም አገልግሎት ነው፤

፮/ "**አበል**" ማለት የአገልግሎት ጡረታ አበል፣ የጤና ጉድለት ጡረታ አበል፣ የጉዳት ጡረታ አበል ወይም የተተኪዎች ጡረታ አበል ሲሆን የዳረጎት አበልን ይጨምራል፤

፯/ "**ደመወዝ**" ማለት ለሥራ ግብርና ለማንኛውም ሌላ ጉዳይ ተቀናሽ የሚሆነው ሂሣብ ሳይነሣለት አንድ የግል ድርጅት ሠራተኛ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከፈለው ሙሉ የወር ደመወዝ ነው፤

፰/ "**ባለመብት**" ማለት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት አበል የሚያገኝ ወይም አበል ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ የግል ድርጅት ሠራተኛ ወይም ተተኪ ነው፤

፱/ **"ተተኪ"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፱ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተዘረዘሩት ናቸው፤

፲/ "**የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ**" ማለት በዚህ አዋጅ ለሚሸፈኑ የግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ አበል ክፍያና አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ ሥርዓት ነው፤

፲፩/ **"የጡረታ ፈንድ"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚሰበሰብ የጡረታ መዋጮና ለሚፈጸም የጡረታ አበል ክፍያ ተግባር የተቋቋመ የግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ ፈንድ ነው፤

፲፪/ "**አስተዳደር**" ማለት ይህን አዋጅ እንዲያስፈጽም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የግል ድርጅት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ፈንድ አስተዳደር ነው፤

፲፫/ "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

5/"**Private Organization Service**" means service rendered by employees of private organizations;

6/ "**Benefit**" means retirement pension, invalidity pension, incapacity pension or survivors' pension and includes gratuity pension;

7/ "**Salary**" means monthly salary received by the employees of private organization, for services rendered during regular working hours without the deduction of any amounts in respect of income tax and any other matter;

8/ "**Beneficiary**" means an employee of private organization or his survivor who receives benefits or fulfills the conditions for receiving benefits in accordance with this Proclamation;

9/ "**Survivors**" means persons mentioned under Article 39(3) of this Proclamation;

10/ "**Private Organization Employees' Pension Scheme**" means a system established to pay benefit and provide service to employees covered by this Proclamation;

11/ "**Pension fund**" means a fund established for the purpose of collecting pension contributions and effecting benefit payments pursuant to this Proclamation;

12/ "**Administration**" means Private Organization Employees Social Security Fund Administration to be established by the Council of Ministers Regulation;

13/ "**Person**" mean any natural or juridical person;

https://chilot.me



፲፬/ በወንድ ፆታ የተገለጸው አገላለጽ የሴትንም ያካትታል::

## ፫. የተፈጻሚነት ወሰን

፩/ የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን የጡረታ ጥቅም የሚመለከተው የአዋጅ ቁጥር ፪፻፸/፲፱፻፺፬ ድንጋጌ እና ሀገሪቷ ተዋዋይ ወገን የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ይህ አዋጅ በዜግነት ኢትዮጵያዊ በሆኑ የግል ድርጅት ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ በሚጠራ ዐቅድ ተጠቃሚ የነበሩ ሠራተኞች በአጠቃላይ በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ የሚሸፈኑ ይሆናል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሠናል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የሃይማኖት ድርጅት እና የፖለቲካ ድርጅት ሠራተኞች እና መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ሰዎች በፈቃደኝነት ላይ ተመሥርቶ በዚህ አዋጅ መሠረት የጡረታ ሽፋን እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ይህ አዋጅ፡-

ሀ) በቤት ሠራተኞች፤

ለ) መንግሥታዊ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የውጭ መንግሥታት ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ሠራተኞች፤

ሐ) በስማቸው ድርጅት ከፍተው የሚያሠሩ የስራ መሪዎች ወይም ሠራተኞች ወይም የግል ድርጅት ባለቤቶች፤

ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

14/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of Application

1/Without prejudice to the appropriate provisions of the Proclamation No. 270/2002 that provide pension coverage to foreign nationals of Ethiopian origin and international agreements to which the country is a party, this Proclamation shall be applicable to employees of private organizations who are Ethiopian nationals.

2/ All employees, who have provident fund or any other scheme called by any other name before the coming into force of this Proclamation, shall be covered by this scheme. The administration may issue the details by the Directive.

3/ Notwithstanding Sub-Article 1 of this Article, employees of religious organizations and political organizations and persons engaged in the informal sector shall, upon their consent, be covered by this Proclamation.

4/ notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, this Proclamation shall not be applicable to:

a) Domestic workers;

b) Employees of governmental international organizations and foreign diplomatic missions; and

c) Sole owner’s managers or employee or Sole owner’s.

https://chilot.me



## ክፍል ሁለት

## ስለማኅበራዊ ዋስትና ምዝገባና መለያ ቁጥር

### ፬. ምዝገባ

፩/ ማንኛውም የግል ድርጅት የተቋቋመበትን ሕግ፣ የግል ድርጅት ሠራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር የሞላውን የግል፣ የአገልግሎትና የቤተሠብ ሁኔታ መግለጫ ቅጽ ፣ የተሠጠውን የቅጥር ደብዳቤ እና ሌሎች በአስተዳደሩ የሚወሠኑ መረጃዎችን ለምዝገባ ለአስተዳደሩ ማቅረብ አለበት፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አዲስ የተቋቋመ የግል ድርጅት ወይም አዲስ የተቀጠረ የግል ድርጅት ሠራተኛ የምዝገባ ማስረጃ የሚቀርበው ድርጅቱ በተቋቋመ ወይም ሠራተኛው በተቀጠረ በ፷ ቀናት ውስጥ ነው፡፡

### ፭.የማኅበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር

፩/ ማንኛውም የግል ድርጅት ወይም የግል ድርጅት ሠራተኛ የምዝገባ ማስረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ የማኅበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር ይሰጠዋል፡፡ሆኖም አግባብ ባለው የመንግሥት አካል የተሠጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ወይም ብሔራዊ መለያ ቁጥር ካለው እንደአግባቡ ይኸው ቁጥር የማኅበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር ጭምር ሆኖ እንዲያገለግል ሊደረግ ይችላል፤

፪/ ማንኛውም የግል ድርጅት ሠራተኛ የማኅበራዊ ዋስትና ሽፋን ባለው የግል ድርጅት ሲቀጠር የማኅበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥሩን ለተቀጠረበት የግል ድርጅት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## PART TWO

## SOCIAL SECURITY REGISTRATION AND IDENTIFICATION NUMBER

### 4. Registration

1/ Any private organization shall, for the purpose of registration, submit to the Administration copies of its establishment law, personal, service and family data registration form of its employee taken at the time of first employment, letter of employment issued to the employee and other particulars determined by the Administration;

2/ The time limit for submission of data in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall, in the case of new private organizations established or new employees of private organizations employed, within 60 days from the date of or employment.

### 5. Social Security Registration Identification Number

1/ Any private organization or an employee shall, upon submission of complete data for registration, be assigned with social security identification number; provided, however, that the tax identification number or national identification number given by authorized government body if any, shall also be taken as social security identification number as the case may be;

2/Any employee, when employed by another private organization covered by social security scheme shall notify his identification number to such office or organization.

https://chilot.me


**፮. የምዝገባ መረጃ ለውጥን ስለማሳወቅ**

፩/ ማንኛውም የግል ድርጅት የራሱንና የግል ድርጅት ሠራተኛውን የምዝገባ መረጃ የሚመለከት ለውጥ ሲያጋጥም ለውጡ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ በ፷ ቀናት ውስጥ የተከሰተውን ለውጥ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር አያይዞ ለአስተዳደሩ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ እያንዳንዱ የግል ድርጅት ሠራተኛ የተተኪ ሁኔታን የሚመለከት የመረጃ ለውጥ ሲያጋጥመው ከደጋፊ ማስረጃ ጋር ለሚሰራበት የግል ድርጅት በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

፫/ አበል በመቀበል ላይ የሚገኝ ባለመብት የተተኪ ሁኔታን የሚመለከት መረጃው ለውጥ ሲያጋጥመው ለውጡ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ በ፷ቀናት ውስጥ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር ለአስተዳደሩ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም የግል ድርጅት፣የግል ድርጅት ሠራተኛ ወይም ባለመብት የሚመለከት የምዝገባ መረጃ ለውጥ ማሳወቂያ ሲቀርብ የማህበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥሩ መጠቀስ አለበት፡፡

፭/ የማኅበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥር የተሰጠው የግል ድርጅት ሲፈርስ፣ ሲከፋፈል ወይም ከሌላ ጋር ሲቀላቀል፡-

ሀ) ስለመፍረሱ፣የፈረሰዉ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የነበረው ወይም አጣሪው፤

ለ) ስለመከፋፈሉ ወይም ስለመቀላቀሉ፣ሠራተኞቹን የተረከበው የግል ድርጅት፤

ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ፷ ቀናት ውስጥ ይህንኑ ለአስተዳደሩ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

**6. Notification of Changes in Entries of Registration**

1/ Any private organization shall, when change of entry of its organization or employee occurs, notify such change to the Administration, with supporting evidence, within 60 days of the occurrence of such change.

2/ Every employee shall notify, with supporting evidence, to the private organization that he is working for, any change regarding his survivor’s status.

3/ Any beneficiary who is receiving benefit shall notify, with supporting evidence, to the Administration any change of survivors status in the entries of social security registration within 60 days of the occurrence of such change.

4/ any notification of change in the entry of social security registration relating to a private organization, employee or beneficiary shall indicate the corresponding social security identification number.

5/ Where a private organization to which a social security registration identification number is assigned has been dissolved, divided or amalgamated.

a) The former Director or the liquidator, in the case of dissolution;

b) The private organization to which employees have been transferred, in the case of division or amalgamation;

Shall notify same to the administration, with supporting document, within 60 days from the date of the decision to such effect:

https://chilot.me


**፯. ማስረጃን አለማቅረብ የሚያስከትለው ውጤት**

፩/ በዚህ ክፍል በተመለከተው መሠረት የሠራተኛ ማስረጃ አደራጅቶ የማይዝና በወቅቱ ለአስተዳደሩ የማያስተላልፍ የግል ድርጅት የሚመለከተዉ ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፩ መሠረት ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ ክፍል በተመለከተው መሠረት የለውጥ ማስረጃን በወቅቱ ለማያቀርብ የግል ድርጅት ሠራተኛ ወይም ባለመብት ለተተኪው አበል የሚወሰነው ተተኪው አስቀድሞ በአስተዳደሩ ተደራጅቶ በተያዘው መረጃ ተመዝግቦ የሚታወቅ ሲሆን ነው፡፡

**7. Consequences of Failure to Submit Data for Registration**

1/ The concerned officer of a private organization, who fails to organize, keep and timely submit data to the Administration for registration as provided under this Part shall be punishable in accordance with Article 61 of this Proclamation.

2/ Where an employee or beneficiary fails to submit timely data relating to changes in survivors status entries of registration as provided under this Part, his survivors' entitlements to benefits shall be based on the survivor registration data that have already been organized and kept by the Administration.

## ክፍል ሦስት
## ስለጡረታ ዐቅድ፣ፈንድና መዋጮዎች

**፰. ስለ ጡረታ ዐቅድ መቋቋም**

የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**፱. ስለ ጡረታ ፈንድ መቋቋም**

የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**፲. የግል ድርጅት ሠራተኞች አገልግሎት ጡረታ ፈንድ መዋጮዎች**

ለግል ድርጅት ሠራተኞች አገልግሎት ጡረታ ፈንድ በሠራተኛው ደመወዝ ላይ ተመስርቶ የሚደረገው መዋጮ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

፩/ በግል ድርጅቱ ፲፩ በመቶ፤

፪/ በግል ድርጅት ሠራተኛው ፯ በመቶ፡፡

## PART THREE
## PENSION SCHEME, FUND AND CONTRIBUTIONS

**8. Establishment of Pension Scheme**

Private Organization Employees' Pension Scheme is here by established.

**9. Establishment of Pension Fund**

Private Organization Employees' Pension Fund is here by established.

**10. Contribution to the Private Organization Employees' Service Pension Fund**

The contributions payable to the Private Organizations employees' service Pension Fund shall, based on the salary of the employee of the private organization, be:

1/ by the employer, 11%;

2/ by the employee, 7%.

https://chilot.me



**፲፩. ስለጡረታ መዋጮ ገቢ አሰባሠብ**

የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ መዋጮ፣ ወለድና ቅጣት የሚሠበሠበው በፌደራል ደረጃ በገቢዎች ሚኒስቴር፣ በክልሎች በገቢዎች ቢሮ ወይም ግብር እና ታክስ እንዲሠበስብ በሕግ ተቋቁሞ በሌላ ስያሜ በሚጠራ ተቋም ይሆናል፡፡ዝርዝር አፈጻጸሙ አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሠናል፡፡

**፲፪. የጡረታ መዋጮ ክፍያ**

፩/ እያንዳንዱ የግል ድርጅት የሠራተኞቹን የጡረታ መዋጮ ከደመወዛቸው ቀንሶና የራሱን መዋጮ ጨምሮ ለጡረታ ፈንዱ በየወሩ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተገለጸው የጡረታ መዋጮ ለሠራተኞች የወር ደመወዝ ከሚከፈልበት ወር መጨረሻ ቀን አንስቶ በ ፴ ቀናት ውስጥ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

፫/ ከሠራተኞቹ ደመወዝ ሊቀነስ የሚገባውን መዋጮ ሳይቀንስ የቀረ የግል ድርጅት ክፍያውን ራሱ ለመፈጸም ኃላፊ ይሆናል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ተገቢውን የጡረታ መዋጮ የወሩ ደመወዝ ከሚከፈልበት ወር ቀጥሎ፣ የደመወዝ ጭማሪ ሲሆን የደመወዝ ጭማሪው ከተወሠነበት ወር ቀጥሎ ባለው ፴ ቀን ውስጥ፣ ገቢ ያላደረገ የግል ድርጅት ገቢ ባልተደረገው የጡረታ መዋጮ ላይ ደመወዝ ከሚከፈልበት ወይም የደመወዝ ጭማሪው ከተወሠነበት ወር ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ በባንክ ማስቀመጫ ወለድ መጠን መሠረት የሚታሠብ ወለድ እና በየወሩ ፭ በመቶ ቅጣት ይከፍላል፡፡ሆኖም ቅጣቱ ድርጅቱ ከሚፈለግበት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ አጠቃላይ

**11. Pension Contribution Collection**

The private organization employees' pension fund contribution, interest and penalty shall be collected by the Federal Ministry of Revenue, by the Regions Revenue Authority or an Authority legally established for the collection of revenue and tax and called by any other name. The detail is issued by the Directive of the Administration.

**12. Payment of Pension Contributions**

1/Every private organization shall deduct contributions of its employees from their salaries and pay the amount, together with its own contributions to the Pension Fund monthly.

2/ The contributions referred to in Sub-Article (1) of this Article shall be paid to the Pension Fund within 30 days from the last day of the month in which payment of salary shall be effected.

3/ Where the private organization fails to deduct contributions of its employees from their salaries, it shall be liable for payment of same.

4/ If the private organization fails to pay pension contribution collected pursuant to Sub-Article (1) of this Article within 30 days the salary shall be effected or if it is a salary increment after the decision of the increment, it shall be liable to pay interest with the bank deposit interest rate including monthly 5% penalty for the unpaid pension contribution calculated from the first day of the month following the last day of the month in which payment of salary will be effected or the salary

https://chilot.me



ዕዳ ሊበልጥ አይችልም፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፬) ድንጋጌ ይህ አዋጅ ፀንቶ በስራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ ላልተከፈለ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ የተከፈለው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ጀምሮ ባልተከፈለ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ላይ የቅጣት ገደቡ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፮/ ከግል ድርጅቶችና ከግል ድርጅት ሠራተኞች የሚሠበሠው የጡረታ መዋጮ፣ ወለድና ቅጣት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ላይ ሥልጣን የተሠጣቸው ተቋማት በኩል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተሰብስቦ በቀጣዩ ወር የመጀመሪያዎቹ ፲ የስራ ቀናት ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ይደረጋል፡፡

፯/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ላይ ሥልጣን የተሠጣቸው ተቋማት የማይደርሱበትን የጡረታ መዋጮ ክፍያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አስተዳደሩ ራሱ ሊሠበስብ ወይም ለሌሎች አካላት ውክልና በመስጠት መዋጮው እንዲሠበሠብ ማድረግ ይችላል፡፡

፰/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሠበሠበው የጡረታ መዋጮ በትክክልና በወቅቱ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ስለመደረጉ የመከታተልና የመቆጣጠር፣ የጡረታ መዋጮ በሚሠበስበው አካል እና በግል ድርጅቶች በመገኘት ወይም ማስረጃ በማስቀረብ ምርመራ(ኦዲት) በማድረግ የማጣራት እንዲሁም በተገቢው ጊዜ ገቢ በማያደርጉት ላይ ሕጋዊ እርምጃ የመውሰድ ስልጣን ይኖረዋል፡፡

increment is decided. However the total penalty shall not be greater than the total debt of the pension contribution.

5/ Without prejudice the penalty already paid for the arrears,the provisions of Sub-Article (4) of this Article shall apply to the arrears arising from July 8, 2015, subject to the penalties for unpaid arrears prior to the enactment of this Proclamation.

6. Contributions of private organizations and employees of private organization, interest and penalty shall be collected within the time specified under Sub-Article (2) of this Article by the bodies mentioned under Article 11 of this Proclamation and shall be paid to the Pension Fund within the first 10 working days of the following month.

7/ If necessary, the pension contribution that cannot be reached by bodies mentioned under Article 11 of this proclamation, may collect by the Administration itself or by any other body delegated by the Administration.

8/ Pursuant to this Article, the Administration for the proper computation of contributions to be collected and timely paid to the pension fund, shall have the power to supervise, control and make an Audit private organizations and authorized bodies to collect pension contribution, in their office or by asking to provide relevant documents of the pension contribution collected and, to take a legal action if they fail to pay with in the given time.

https://chilot.me


፱/አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ላይ ሥልጣን የተሠጣቸው ተቋማት ወይም የጡረታ መዋጮ ገቢ እንዲሠበስብ ውክልና የተሠጠው አካል ተገቢውን የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ሳያደርግ ከሶስት ወር በላይ የቆየን የግል ድርጅት ዕዳ በባንክ ወይም በፋይናንስ ተቋም ካለው ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ እንዲሆን የማስደረግ ሥልጣን አለው፡፡

፲/ ማንኛውም ባንክ ወይም የፋይናንስ ተቋም በአስተዳደሩ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ላይ ሥልጣን የተሠጣቸው ተቋማት ወይም የጡረታ መዋጮ እንዲሠበስብ ውክልና በተሠጠው አካል ሲጠየቅ ከግል ድርጅቱ የሚፈለገውን የጡረታ መዋጮ ወለድና ቅጣት ዕዳ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከግል ድርጅቱ ሂሳብ ላይ ቀንሶ ለጡረታ መዋጮ ገቢ መሠብሠቢያ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፲፩/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፱) መሠረት ባንኩ ወይም የፋይናንስ ተቋሙ ከድርጅቱ የባንክ ሂሳብ ወይም በፋይናንስ ተቋም የተከፈተ ሂሳብ ላይ የጡረታ መዋጮ ገንዘብ ቀንሶ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ እንዲያደርግ በአስተዳደሩ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ላይ ስልጣን በተሠጣቸው ተቋማት ወይም ውክልና በተሠጠው አካል በጽሁፍ ከተገለጸለት በኋላ ከድርጅቱ የባንክ ወይም በፋይናንስ ተቋም ከተከፈተ ሂሳብ ላይ ገንዘብ ወጪ ሆኖ ቢገኝ ወጪ በተደረገው ገንዘብ መጠን ልክ ወይም እንደ አግባቡ በቀረው ዕዳ መጠን ባንኩ ወይም የፋይናስ ተቋሙ ኃላፊ ይሆናል፡፡

፲፪/ በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ለተሸፈኑ ሠራተኞች ደመወዝ የሚከፍል አሠሪ ገንዘቡ የሚገኝበትን የባንክ ቅርንጫፍና የሂሣብ ቁጥሩን ለአስተዳደሩ በጽሁፍ የማሳወቅ፣የባንኩ አድራሻና የሂሣብ ቁጥሩ ሲለወጥም ለውጡ ከተከሰተበት ቀን

9/ Where a private organization fails to pay contributions for a period of more than three months, the Administration, authorized bodies under Article 11 of this Proclamation or the delegated body has the power to cause the deduction of the debt from its bank or financial institution account.

10/ Any bank or financial institution shall, when requested by the Administration, authorized bodies under Article 11 of this Proclamation or the delegated body, have the obligation to deduct, without any precondition, the debt of contributions, penalty and interest from the account of the private organization and deposit to the pension contribution collection bank account.

11/ According to Sub-Article (9) of this Article, after written instruction of the Adminstration, authorized bodies under Article 11 of this Proclamation or the delegated body, the bank or financial institution permit to withdraw any amount of money from the account of such private organization, before the settlement of the debt, the bank or financial institution as the case may be is responsible to the extent the amount withdrawn or the remaining debt.

12/ A private organization which pays salary to employees covered by pension scheme shall have an obligation to notify in a written form, to the Administration the branch of the bank and the account number in which it

https://chilot.me



አንስቶ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ለአስተዳደሩ በጽሁፍ የመግለጽ ግዴታ አለበት፡፡

፲፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ሊሠበሠብ ያልቻለን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ፣ ወለድና ቅጣት የጡረታ መዋጮ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ የግል ድርጅቶችን ሃብት የሚያዝበትን እና የጡረታ መዋጮ ገቢ አሠባሠብ የሚከናወንበትን ሥርዓት አስመልክቶ አስተዳደሩ መመሪያ ያወጣል፡፡ አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ላይ ስልጣን የተሠጣቸው ተቋማት ወይም የጡረታ መዋጮ ገቢ እንዲሠበስቡ ውክልና የተሠጣቸው አካላት ይህንኑ መመሪያ በመከተል የጡረታ መዋጮ ዕዳ ወለድና ቅጣት እንዲሠበስቡ ስልጣን ተሠጥቷቸዋል፡፡

፲፬/ ከጡረታ መዋጮ ገንዘብ ላይ ቀንሶ ለአገልግሎት ክፍያ፣ ለገንዘብ ማስተላለፊያ፣ ለዕዳ ወይም ለማንኛውም አገልግሎት መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

፲፭/ የጡረታ መዋጮ ክፍያ ከቅጥር የሚመነጭ የሠራተኛው የማኅበራዊ ዋስትና ክፍያ በመሆኑ ከሕግ፣ ከውል ወይም ከፍርድ ከሚመነጭ ወይም ከሌላ ማናቸውም ዕዳ ክፍያ ቅድሚያ ይኖረዋል፡፡

፲፮/ ማንኛውም የግል ድርጅት የሚፈለግበትን የጡረታ መዋጮ ሙሉ በሙሉ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ስለማድረጉ የጡረታ መዋጮ ገቢ እንዲሠበስቡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ላይ ሥልጣን በተሠጣቸው አካላት ማረጋገጫ ክሊራንስ ካልተሠጠው በስተቀር ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የተሠጠው ማንኛውም ዓይነት ፈቃድ አይታደስለትም፡፡

has deposited money, and any change of address of the bank and bank account within 15 days of the occurrence of such change.

13/ For pension contribution that unable to collect pursuant to this Article the Administration may issue the Directive of seizing the property of private organization that failed to discharge its obligation to pay pension contribution. The Administration, authorized bodies under Article 11 of this Proclamation or the delegated body shall have the power to collect the pension contribution, penalty and interest in line with the Directive issued by the Administration.

14/ It is prohibited to deduct from pension contributions for payment of service charges, money transfer charges or debt or for any other purpose.

15/ Since pension contribution Payment emanates from employment agreement and it is the social security payment for the employees, the payment of pension contributions shall have priority emanate from the law, agreement, or court decision or over any payment of debt.

16/ Any private organization unless provide clearance for the full payment of pension contribution from the authorized body to collect pension contribution under Article 11 of this Proclamation, any license given by the authorized government body shall not be renewed.

https://chilot.me



፲፯/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ-አንቀጽ (፭) መሠረት የፈረሠ፣ የተከፋፈለ ወይም የተቀላቀለ የግል ድርጅት ስራ አስኪያጅ ድርጅቱ ለሚፈለግበት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ኃላፊ ይሆናል፡፡

17/ The General Manager of a private organization which has been dissolved, divided or amalgamated, pursuant to Sub-Article (5) of Article 6 of this Proclamation ,is liable` for the unpaid arrears pension contribution.

## ፲፫ **የጡረታ ፈንድ አስተዳደር**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ የተቋቋመውን የጡረታ ፈንድ የሚያስተዳድረው አስተዳደሩ ይሆናል፡፡

## 13. **Administration of Pension Fund**

The Pension Fund established under Article 9 of this Proclamation shall be administered by the Administration.

## ፲፬. **የጡረታ ፈንድ አጠቃቀም**

፩/ የጡረታ ፈንዱ ጥቅም ላይ የሚውለው፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን የጡረታ አበል ክፍያዎች ለመፈጸም፤

ለ) በአስተዳደሩ ሥራ አመራር ቦርዱ ለሚወሠኑ አትራፊና አስተማማኝ ኢንቨስትመንቶችን ስራ ላይ ለማዋል፤ እና

ሐ) ለአስተዳደሩ አስተዳደራዊ ወጪዎች፤

ብቻ ይሆናል፤

፪/ የጡረታ ፈንዱ በማናቸውም የዕዳ ክፍያ ምክንያት ሊከበር ወይም ሊያዝ አይችልም፡፡

## 14. **Utilization of Pension Fund**

1/ The Pension Fund shall be utilized only for:

a) Effecting benefit payments stipulated in this Proclamation;

b) For running cost of profitable and reliable investments specified by the Administration's management board; and

c) The administrative expenses of the administration.

2/ The Pension Fund may not be attached or secured in respect of any debt.

## ፲፭. **የአክችዋሪ ግምገማ**

፩/ አክችዋሪ ግምገማ ማለት የጡረታ ዐቅድ ስታስቲካዊ መረጃዎች፣ የኢንቨስትመንት አፈፃፀምን፣ የኢኮኖሚ እና ሥነ-ህዝባዊ ግምታዊ መረጃዎችን በማጠናቀርና በመተንተን የጡረታ ፈንዱ ያለበት ደረጃ የሚለይበት፣ ስጋቶች እና የወደፊት ሁኔታ ትንበያ የሚከናወንበት የግምገማ ዘዴ ነው፡፡

፪/ የጡረታ ዐቅዱ በየአምስት ዓመቱ በሂሣብ ስሌት ባለሙያዎች እንዲገመገም ይደረጋል፡፡

## 15. **Actuarial Analysis and Evaluation**

1/ "Actuarial Valuation" is a method of compiling and analyzing the pension scheme's statistical data, investment performance, economic and demographic estimates, and identifying the pension fund status, risk and future projections.

2/ The Pension Scheme shall be evaluated by actuaries every five years.

https://chilot.me


## ክፍል አራት

## ስለአገልግሎት ዘመንና የጡረታ መውጫ ዕድሜ

**፲፮. የአገልግሎት ዘመን መቆጠር ስለሚጀምርበት ጊዜ**

፩/ የግል ድርጅት ሠራተኛው የአገልግሎት ዘመን መቆጠር የሚጀምረው በሠራተኛነት ተቀጥሮ በጡረታ ዐቅድ ከተሸፈነበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

፪/ የግል ድርጅት ሠራተኛው በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ በሚሸፈን የመንግሥት መስሪያ ቤት የፈጸመው አገልግሎት በዐቅዱ መዋጮ መክፈል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ይያዝለታል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ለተጠቀሠው አገልግሎት አያያዝ የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድን የሚያስተዳድረው አካል የሠራተኛውን የግል ማስረጃ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድን ለሚያስተዳድረው አካል ማስተላለፍ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ለተፈጸመ አገልግሎት አያያዝ ከመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ወደ ግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ እንዲሁም በግል ድርጅት ለተፈጸመ አገልግሎት አያያዝ ከግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ወደ መንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ የሚደረገውን የጡረታ መዋጮ ገንዘብ ትልልፍ በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሠናል፡፡

**፲፯. የአገልግሎት ዘመን አቆጣጠር**

፩/ የአገልግሎት ዘመን የሚቆጠረው በሙሉ ዓመታት፣ በወራትና በቀናት ታስቦ ነው፡፡

## PART FOUR

## PERIOD OF SERVICE AND RETIREMENT AGE

**16. Commencement of Period of Service**

1/ The period of service of employee shall begin with the date of his employment covered by pension scheme.

2/ The service that an employee of a private organization rendered to public offices covered by the pension scheme shall be counted starting from the date of pension contribution payment.

3/ For the purpose of service counting pursuant to Sub-Article (2) of this Article, the organ which administers the Public Servants Pension Scheme shall transfer, within one month, the personal records of the employee to Private Organizations Employees' Pension Scheme.

4/ Subject to the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the issue of transfer of pension contributions from the Public Servants Pension Fund to the Private Sector Employees 'Pension Fund and the transfer of funds from the Private Sector Employees' Pension Fund to the Public Servants Pension Fund shall be determined based on the Directives issued by the National Bank.

**17. Calculation of Period of Service**

1/ Period of service shall be calculated in complete years, months and days.

https://chilot.me



፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ ዐቅድ ሽፋን ባላቸው የግል ድርጅቶች የተፈጸመ የአገልግሎት ዘመን በሙሉ ተደምሮ ይታሰባል፡፡

፫/ ለማንኛውም የግል ድርጅት ሠራተኛ የሚከተለው አገልግሎቱ ይታሰብለታል፡-

ሀ) የደመወዝ ክፍያ ሳይቋረጥ በማናቸውም ምክንያት አገልግሎቱ ተቋርጦ የቆየበት ጊዜ፤

ለ) በየወሩ ደመወዝ እየተከፈለው ሙሉ ጊዜውን በማናቸውም የመንግሥት አካል በሕዝብ ወይም በሠራተኛ ማኅበር በተመራጭነት አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ በንዑስ አንቀጽ (፬)(ለ) የተደነገገዉ ቢኖርም በመንግሥት ውሳኔ በዓለም አቀፍ ድርጅት በማገልገል ያሳለፈው ጊዜ፡፡

፬/ ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን የሆነችበት ማናቸውም ዓለም አቀፍ ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሕጋዊ ፈቃድ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነ የግል ድርጅት ሠራተኛ የኢትዮጵያን ዜግነት ከማግኘቱ በፊት በግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ የግል ድርጅት የሰጠው የአገልግሎት ዘመን አይታሰብለትም፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) (ለ) እና (ሐ) የተመለከተው ጊዜ በአገልግሎት ዘመንነት ሊታሰብ የሚችለው የግል ድርጅት ሠራተኛው መከፈል ያለበትን የጡረታ መዋጮ የአሰሪውን ድርሻ ጨምሮ ራሱ የከፈለ ወይም እንዲከፈልለት ያደረገ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

2/ Without prejudice to the provisions of Article 16 of this Proclamation, the period of service of an employee shall include all services rendered in a private organization covered by the Pension Scheme.

3/ for any employee the following shall be counted as period of service:

a) Period of service which was interrupted without interruption of payment of salary;

b) Period of service spent in any public body by the public or labour union elected member;

c) Notwithstanding the provision of Sub-Article (4) (b) of Article 3 of this Proclamation, period of service spent, upon a government decision, in an international organization.

4/ without prejudice to any international agreement to which Ethiopia is a party, the service rendered by naturalized Ethiopian in any private organization covered by the private organizations employees' pension Scheme before his naturalization shall not be counted.

5/ Period of service referred to under Sub-Article (3) (b) and (c) of this Article shall be counted for a period of service only where the employee pays the contributions by himself including that of the employer or causes the employer to effect payments of same.

https://chilot.me



፮/ በዚህ አዋጅ ወይም በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ዳረጎት ተከፍሎት የስራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ እንደገና በግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ የግል ድርጅት የተቀጠረ ከሆነና የወሰደውን ዳረጎት መልሶ ገቢ ካደረገ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞው አገልግሎቱ ይታሰብለታል፡፡

፯/ በዚህ አዋጅ ወይም በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ተደርጎለት የነበረ ሰው እንደገና በግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ የግል ድርጅት ውስጥ ከተቀጠረ እና መጦሪያ ዕድሜ ላይ ከመድረሱ አስቀድሞ የወሰደውን መዋጮ ከባንክ የማስቀመጫ ወለድ ጭምር ተመላሽ ካደረገ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞው አገልግሎቱ ይታሰብለታል፡፡

፰/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስተዳደሩ በሚያቀርብለት ጥናት መሠረት በከባድ ወይም ለጤንነትና ለሕይወት አስጊ በሆኑ የሥራ መስኮች የተፈጸመ አገልግሎት እስከ አጠፌታ እንዲቆጠር ሊወስን ይችላል፡፡

## ፲፰. የጡረታ መውጫ ዕድሜ

፩/ የጡረታ መውጫ ዕድሜ የግል ድርጅት ሠራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር በቅድሚያ የመዘገበውን የልደት ዘመን መሠረት በማድረግ ፷ ዓመት ይሆናል፡፡

6/ Where an employee who has received retirement or invalidity gratuity pursuant to this Proclamation or public servant pension proclamation is re-employed as an employee of a private organization covered by the Private Organizations Employees' Pension Scheme, his former service shall, without prejudice to Article 16 of this Proclamation, be counted along with the new service; provided that the gratuity is paid back.

7/ A person to whom reimbursement of pension contribution has been made before the coming in to force of this Proclamation or the public servant pension Proclamation, if employed as an employee of private organization covered by the Private Organizations Employees' Pension Scheme, before retirement age his former service shall, without prejudice to Article 16 of this Proclamation, be counted along with the new service; provided, however, that the reimbursed contribution is paid back with interest calculated at bank deposit interest rate.

8/ On the basis of studies submitted to it by the Administration, the Council of Ministers may decide that period of service spent on hazardous jobs or on jobs involving risk to health and life be counted up to twice the actual period of service.

## 18. Retirement Age

1/ The retirement age of an employee shall be 60 years based on the date of birth registered when he was employed for the first time.

https://chilot.me


፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተገለጸው ውጪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በቅድሚያ የተመዘገበን ዕድሜ ወይም የልደት ዘመን ለመቀየር ወይም ለማሻሻል የሚቀርብ ማንኛውም ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

፫/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስተዳደሩ በሚያቀርብለት ጥናት መሠረት በልዩ ሁኔታ ለሚታዩ የሙያ መስኮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው በላይ የሆነ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሊወስን ይችላል፡፡

፬/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስተዳደሩ በሚያቀርብለት ጥናት መሠረት በከባድ ወይም ለጤንነትና ለሕይወት አስጊ በሆኑ የሥራ መስኮች ላይ ለተሰማሩ የግል ድርጅት ሠራተኞች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው ያነሰ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሊወስን ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት
## ስለአገልግሎት ጡረታ አበልና ዳረጎት

### ፲፱ የአገልግሎት ጡረታ አበል

፩/ ቢያንስ ፲ ዓመት ያገለገለ የግል ድርጅት ሠራተኛ አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሲደርስ የጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፡፡

፪/ ቢያንስ ፳፭ ዓመት ያገለገለ የግል ድርጅት ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጭ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሊደርስ አምስት ዓመት ከሚቀረው ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕድሜ ልኩ የአገልግሎት ጡረታ አበል ይከፈለዋል፡፡

2/ Excluding as specified under Sub-Article (1) of this Article, any evidence submitted to change or modified the pre-registered age or date of birth in accordance with Sub-Article (1) of article 4, and Sub-Article (1) of Article 6 of this Proclamation shall not be accepted.

3/ On the basis of studies submitted to it by the Administration, the Council of Minister may determine higher retirement age than the age provided for under Sub-Article (1) of this Article with respect to professions that may deserve special consideration.

4/ On the basis of studies submitted to it by the Administration, the Council of Ministers may decide retirement age lesser than the age provided for under Sub-Article (1) of this Article for employees of private organizations working on hazardous jobs or on jobs involving risks to health and life.

## PART FIVE
## RETIREMENT PENSION AND GRATUITY

### 19. Retirement Pension

1/ An employee of a private organization who has served for at least 10 years, if terminate his contract of employment, he shall receive retirement benefit for life up on attaining retirement age.

2/ An employee who has completed at least 25 years of service and separates from the service by voluntary resignation or for any other causes other than those provided for in this Proclamation shall receive retirement pension for life beginning with five years prior to retirement age.

https://chilot.me



፫/ እድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ መብት መከበሩ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ በዲስፕሊን ጉድለት ምክንያት አገልግሎቱ ለተቋረጠ የግል ድርጅት ሠራተኛ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣(፪) ወይም(፫) መሠረት አገልግሎቱ የተቋረጠ የግል ድርጅት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሳይደርስ በጤና ጉድለት ምክንያት ለሥራ ብቁ አለመሆኑ በህክምና ቦርድ ከተረጋገጠ ይኸው ከተረጋገጠበት ጊዜ ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፤ የሞተ እንደሆነም ከሞተበት ጊዜ ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ ለተተኪዎች አበል ይከፈላል፡፡

## ፳. የአገልግሎት ጡረታ አበል መጠን

፩/ ለማንኛውም ፲ ዓመት ላገለገለ የግል ድርጅት ሠራተኛ የሚከፈለው የአገልግሎት ጡረታ አበል መጨረሻ በገለገለባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ይከፈለው የነበረው አማካይ ደመወዝ ፴ በመቶ ሆኖ ከ፲ ዓመት በላይ ለፈጸመው ለእያንዳንዱ ዓመት አገልግሎት ፩ ነጥብ ፳፭ በመቶ ተጨምሮ ይታሰባል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የግል ድርጅት ሠራተኛው በጡረታ ከሚገለልበት ወር ሦሥት ዓመት አስቀድሞ ባለው ወር ሲከፈለው ከነበረው የጡረታ መዋጮ የተከፈለበት መደበኛ የወር ደመወዝ በ፳፭ በመቶ የሚበልጥ አመታዊ አማካኝ የደመወዝ ክፍያ ያገኘ እንደሆነ በየዓመቱ እስከ ፳፭ በመቶ ያለው የደመወዝ ክፍያ ብቻ በደመወዙ ላይ ተደምሮ የሦሥት አመት አማካይ የወር ደመወዙ ተይዞ ይታሰባል፡፡

3/ Without prejudice to the entitlement of pension right up on attainment of retirement age, the provisions of Sub-Article (2) of this Article shall not be applicable to an employee who separates from the service on grounds of disciplinary measures.

4/ Where it is ascertained that an employee who has separated from service in accordance with Sub-Article (1), (2) or (3) of this Article due to health problem which prevent him from engaging in any remunerated work prior to attaining the retirement age he shall receive retirement pension for life starting with the month following such ascertainment by the medical board; in case he dies, his survivors shall be paid benefits starting with the month following his death.

## 20. Amount of Retirement Pension

1/ The retirement pension due to any employee shall be 30% of his average salary of the last three years preceding retirement and shall be increased by 1.25% for each year of service beyond 10 years.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, an employee who is employed in a private organization if paid more than 25% annual average salary payment on the salary that pension contribution was paid a month before 3 years of his pension entitlement, the 25% annual average salary payment shall only be considered for the calculation of three years average monthly salary;

https://chilot.me



፫/ በመከላከያ ሠራዊት ወይም በፖሊስ አባልነት አገልግሎት ለፈጸመ የግል ድርጅት ሠራተኛ ይኸው አገልግሎቱ በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ለመከላከያ ሠራዊት እና ለፖሊስ አባል በተቀመጠው የስሌት ቀመር መሠረት ተሠልቶና ተዳምሮ ይታሰብለታል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ ንዑስ-አንቀጽ (፫) በተደነገገው መሠረት የሚወሰነው የአበል መጠን የግል ድርጅት ሠራተኛው ለጡረታ አበል አወሳሰን ከታሠበው የሰስት አመት አማካይ ደመወዝ ፸ በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

3/ For any private organization employee who has served as a member of the national defense force or as a member of police, the service shall be calculated and added in accordance with the formula set under Public Servant Pension Proclamation;

4/ The retirement pension to be paid pursuant to Sub-Article (1), up to (3) of this Article may not exceed 70% of the average salary calculated for pension benefit entitlement of the employee.

## ፳፩. <u>የአገልግሎት ዳረጎት</u>

ከአሥር ዓመት ያነሰ አገልግሎት የፈጸመ የግል ድርጅት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ ከሥራ ሲሰናበት የአገልግሎት ዳረጎት ይከፈለዋል፡፡

## 21. <u>Retirement Gratuity</u>

An employee who has not completed 10 year of service and retires on attaining retirement age shall receive gratuity.

## ፳፪. <u>የአገልግሎት ዳረጎት መጠን</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ መሠረት የሚከፈለው ዳረጎት የግል ድርጅት ሠራተኛው ከሥራ ከተሰናበተበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የ፩ ነጥብ ፳፭ ወር ደመወዝ በአገለገለበት ዓመት ቁጥር ተባዝቶ ይታሰባል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የግል ድርጅት ሠራተኛው በጡረታ ከሚገለልበት ወር ሦሥት ዓመት አስቀድሞ ባለው ወር ሲከፈለው ከነበረው የጡረታ መዋጮ የተከፈለበት መደበኛ የወር ደመወዝ በ፳፭ በመቶ የሚበልጥ ዓመታዊ አማካኝ የደመወዝ ክፍያ ያገኘ እንደሆነ በየአመቱ እስከ ፳፭ በመቶ ያለው የደመወዝ ክፍያ ብቻ በደመወዙ ላይ ተደምሮ የዳጎት አበሉ ይታሰባል፡፡

## 22. <u>Amount of Retirement Gratuity</u>

1/ The gratuity payable in accordance with Article 21 of this Proclamation shall be his salary for 1.25 month preceding retirement multiplied by the number of years of service.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, an employee who is employed in a private organization if paid more than 25% annual average salary payment on the salary that pension contribution was paid a month before 3 years of his pension entitlement, the 25% annual average salary payment shall only be considered for the calculation of gratuity.

https://chilot.me


## ክፍል ስድስት
## ስለጤና ጉድለት ጡረታ አበልና ዳረጎት

**፳፫. የጤና ጉድለት ጡረታ አበል**

ቢያንስ ፲ ዓመት ያገለገለ የግል ድርጅት ሠራተኛ በጤና ጉድለት ምክንያት ደመወዝ የሚያስገኝ ማናቸውንም ሥራ መሥራት የማይችል መሆኑ ተረጋግጦ ከሥራ ሲሰናበት የጤና ጉድለት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል።

**፳፬. የጤና ጉድለት ጡረታ አበል መጠን**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ መሠረት የሚከፈለው የጤና ጉድለት ጡረታ አበል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ መሠረት ይታሰባል።

**፳፭. የጤና ጉድለት ዳረጎት**

ከአስር ዓመት ያነሰ አገልግሎት የፈጸመ የግል ድርጅት ሠራተኛ በጤና ጉድለት ምክንያት ለሥራ ብቁ ባለመሆኑ ከሥራ ሲሰናበት የጤና ጉድለት ዳረጎት ይከፈለዋል።

**፳፮. የጤና ጉድለት ዳረጎት መጠን**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ መሠረት የሚከፈለው ዳረጎት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ መሠረት ይታሰባል።

## ክፍል ሰባት
## ስለጉዳት ጡረታ አበልና ዳረጎት

**፳፯. ትርጓሜ**

፩/ "በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት" ማለት በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው።

## PART SIX
## INVALIDITY PENSION AND GRATUITY

**23. Invalidity Pension**

Employee who has completed at least 10 years of service and separates from service due to health problems preventing him from engaging in any remunerated work shall receive invalidity pension for life.

**24. Amount of Invalidity Pension**

The invalidity pension payable in accordance with Article 23 of this Proclamation shall be calculated as provided under Article 20 hereof.

**25. Invalidity Gratuity**

An employee who has not completed ten years of service and separates from service on becoming unfit for service due to health problems shall receive invalidity gratuity.

**26. Amount of Invalidity Gratuity**

The gratuity payable in accordance with Article 25 of this Proclamation shall be calculated as provided under Article 22 hereof.

## PART SEVEN
## EMPLOYMENT INJURY PENSION AND GRATUITY

**27. Definition**

1/ "Employment injury" means an occupational accident or occupational disease.

https://chilot.me



፪/ "በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ" ማለት የግል ድርጅት ሠራተኛው መደበኛ ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ወይም ከሥራው ጋር በተያያዘ ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ የተፈጥሮ ተግባር ላይ በድንገት የሚደርስ ጉዳት ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ) የግል ድርጅት ሠራተኛው ከመደበኛ ሥራው ወይም መደበኛ የሥራ ቦታው ወይም ሰዓት ውጪ ሥልጣኑ በሚፈቅድለት የሥራ ኃላፊ የተሰጠውን ትዕዛዝ በመፈጸም ላይ እያለ የደረሰን ጉዳት፤

ለ) ሥልጣኑ በሚፈቅድለት የሥራ ኃላፊ የተሰጠው ትዕዛዝ ባይኖርም የግል ድርጅት ሠራተኛው በግል ድርጅቱ ውስጥ የደረሰን ድንገተኛ አደጋ ወይም ጥፋት ለመከላከል በሥራ ሰዓት ወይም ከሥራ ሰዓት ውጪ በሚፈጽመው ተግባር ምክንያት የደረሰን ጉዳት፤

ሐ) የግል ድርጅት ሠራተኛው ወደ ሥራ ቦታው ወይም ከሥራ ቦታው አሠሪው ለሠራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ወይም አሠሪው ለዚህ ተግባር በተከራየውና በግልጽ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት በመጓዝ ላይ በነበረበት ጊዜ የደረሰን ጉዳት፤

መ) የግል ድርጅት ሠራተኛው ከሥራው ጋር በተያያዘ ግዴታ የተነሣ ከሥራው በፊት ወይም በኋላ ወይም ሥራው ለጊዜው ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ በሥራ ቦታው ወይም በግል ድርጅቱ ግቢ ውስጥ በመገኘት የደረሰበት ማንኛውንም ጉዳት፤

ሠ) የግል ድርጅት ሠራተኛው ሥራውን በማከናወን ላይ ባለበት ጊዜ በአሠሪው ወይም በሦስተኛ ወገን ድርጊት ምክንያት የደረሰበት ጉዳት፡፡

2/ "Occupational accident" means any organic injury or functional disorder suddenly sustained by an employee during or in connection with the performance of his work, and shall include the following;

a) Any injury sustained by an employee of private organization while carrying out orders given by a competent authority outside of his regular work or working place or working hours;

b) Any injury sustained by an employee during or outside of working hours while attempting to protect the private organization from accident or destruction irrespective of an order given by a competent authority;

c) any injury sustained by an employee while he is proceeding to or from his place of work in a transport service vehicle provided by the private organization which is available for the common use of its employees or in a vehicle hired and expressly destined by the organization for the same purpose;

d) any injury sustained by an employee before or after his work or during any interruption of work, if he is present in the work place or the premises of the private organization by reason of his duties in connection with this work;

e) Any injury sustained by an employee as a result of an action of the private organization or a third person during the performance of his work;

https://chilot.me


፫/ "በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ" ማለት የግል ድርጅት ሠራተኛው ከሚሠራው የሥራ ዓይነት ወይም ሥራውን ከሚያከናውንበት አካባቢ የተነሣ በሽታውን ለሚያስከትሉ ሁኔታዎች ተጋልጦ በመቆየቱ ምክንያት የደረሰ የጤና መታወክ ሲሆን ሥራውን በሚያከናውንበት ቦታ የሚዛመቱና የሚይዙ ነዋሪ ወይም ተላላፊ በሽታዎችን አይጨምርም፡፡

፬/ "መደበኛ ሥራ" ማለት የግል ድርጅት ሠራተኛው በተሰጠው ኃላፊነት ወይም የሥራ ውል መሠረት የሚያከናውነው ተግባር ነው፡፡

፭/ "መደበኛ የሥራ ቦታ" ማለት የግል ድርጅት ሠራተኛው የግል ድርጅቱን ሥራ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የሚያከናውንበት ሥፍራ ነው፡፡

**፳፰. በራስ ላይ ጉዳት ስለማድረስ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፯ የተመለከተው ተቀባይነት የሚኖረው የግል ድርጅት ሠራተኛው ጉዳቱ እንዲደርስበት ሆነ ብሎ ያላደረገው ሲሆን ነው፡፡ በተለይም ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የደረሰ ጉዳት የግል ድርጅት ሠራተኛው በራሱ ላይ ሆን ብሎ ያደረሰው ጉዳት ሆኖ ይቆጠራል፡-

፩/ በአሠሪው አስቀድሞ በግልጽ የተሰጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎች መጣስ ወይም የአደጋ መከላከያ ደንቦችን መተላለፍ፤ ወይም

፪/ አካሉን ወይም አእምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ ዕጽ ሰክሮ በሥራ ላይ በመገኘት፤

የደረሰ ጉዳት፡፡

3/ "occupational disease" means any pathological condition of an employee which arises as a consequence of being exposed to the agent that cause the disease for a certain period prior to the date in which the disease became evident due to the kind of work he performs or because of the surrounding in which he works; provided, however, that it does not include endemic or epidemic diseases which are prevalent and contracted in the area where the work is done;

4/ "regular work" means a work performed by an employee pursuant to his assignments or contract of employment.

5/ "regular place of work" means a place where an employee performs his duties for definite or indefinite period.

**28. Self-Inflicted Injury**

The provisions of Article 27 of this Proclamation shall apply only where the employee has not inflicted the injury upon himself intentionally. Any injury resulting from, in particular, the following acts shall be deemed to be intentionally caused by the employee:

1/ non-observance of safety instructions or preventive rules specifically issued by the private organization; or

2/ work in a state of intoxication that prevents him from properly regulating his conduct or understanding.

https://chilot.me



**፳፱. በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታና የአካል ጉዳት መጠን ሠንጠረዥ**

፩/ አስተዳደሩ አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም፡-

ሀ) የአካል ጉዳት መጠን፤

ለ) እያንዳንዱን በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታን በሚመለከት፡-

(፩) የበሽታውን ምልክቶች፤

(፪) ለበሽታው መነሻ ይሆናል ተብሎ የሚታመነውን የሥራ ዓይነት ወይም አካባቢ፤

(፫) በሽታውን ለሚያስይዘው የሥራ ሁኔታ ለመጋለጥ የሚያስፈልገውን አነስተኛ ጊዜ፤

የያዘ ዝርዝር ሠንጠረዥ በመመሪያ ያወጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የወጣው ሠንጠረዥ እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው ይሻሻላል፡፡

**፴. ግምት**

፩/ ከሥራው በታ ወይም ከሥራው ዓይነት ጋር የተያያዘ በሠንጠረዡ ውስጥ የተመለከተ በሽታ በተጠቀሰው የሥራ በታ ወይም የሥራ ዓይነት ላይ የተሰማራን የግል ድርጅት ሠራተኛ የያዘው እንደሆነ በሽታው በሥራ ምክንያት እንደመጣ ይቆጠራል፡፡

፪/ በሥራ ምክንያት በሚመጣ በሽታ ተይዞ የዳነ የግል ድርጅት ሠራተኛ በሰንጠረዡ ውስጥ በበሽታው አንጻር በተመለከተው የሥራ ዓይነት ላይ ተመድቦ መሥራት በመቀጠሉ በዚያው በሽታ እንደገና ቢያዝ አዲስ በሽታ እንደያዘው ይቆጠራል፡፡

**29. Schedule of Occupational Diseases and Degrees of Incapacity**

1/ For the implementation of this Proclamation, the Administration shall, in consultation with the appropriate organ and by Directives, issue a schedule that lists:

a) The degrees of incapacity;

b) With respect to each occupational disease:

(1) The symptoms;

(2) The kind of work or surrounding that gives rise to the disease;

(3) The minimum duration of exposure to the agent causing the disease.

2/ the schedule issued in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be revised periodically as necessary.

**30. Presumption**

1/ Where a disease listed in the schedule is contracted by an employee of private organization engaged in the corresponding work place or kind of work, it shall be presumed an occupational disease.

2/Where an employee who had recovered from an occupational disease is re-infected due to continued placement in the occupation corresponding to the disease listed in the schedule, he shall be presumed to have contracted the occupational disease afresh.

https://chilot.me


፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፯ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው ቢኖርም በመደበኛ ሥራው ምክንያት ተላላፊ ወይም ነዋሪ በሽታዎችን በማጥፋት ላይ የተሰማራ የግል ድርጅት ሠራተኛ በዚሁ በሽታ ከተያዘ በሥራ ምክንያት የመጣ በሽታ እንደያዘው ይቆጠራል፡፡

3/ Notwithstanding Sub-Article (3) of Article 27 of this Proclamation where an employee engaged in the eradication of endemic or epidemic disease contracts same, it shall be presumed an occupational disease.

**፴፩. ማስረጃ ማቅረብ ስለመቻሉ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ መሠረት በሚወጣው ሠንጠረዥ ውስጥ ያልተመለከተ በሽታ በሥራ ምክንያት የመጣ መሆኑን እንዲሁም በሠንጠረዡ ውስጥ የተመለከተ በሽታ በአንጻሩ ከተመለከቱት ምልክቶች በተለየ ሁኔታ የተከሰተ መሆኑን ለማረጋገጥ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል፡፡

**31. Admissibility of Evidence**

Production of evidence may be permitted to proof that a disease not listed in the schedule issued under Article 29 of this Proclamation is of occupational origin, and that a disease listed in the schedule has been manifested in different symptoms from those indicated therein.

**፴፪. አደጋን ስለማስታወቅ**

አንድ የግል ድርጅት ሠራተኛ የሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ የግል ድርጅቱ አደጋው ከደረሰበት ቀን አንስቶ ባሉት ፴ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለአስተዳደሩ ማስታወቅ አለበት፡፡ ይህ ባለመደረጉ በግል ድርጅት ሠራተኛው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የግል ድርጅቱ ኃላፊ ይሆናል፡፡

**32. Notification of Accident**

Where an employee sustains occupational injury, the private organization shall notify, in writing, the occurrence of same to the Administration within 30 days of such occurrence. Failure to do so shall make the private organization liable for the injury sustained by the employee.

**፴፫. ስለአካል ጉዳት መጠን አወሳሰን**

፩/ በሥራ ምክንያት የሚመጣ የጉዳት መጠን የሚወሰነው ሥልጣን በተሰጠው የህክምና ቦርድ ነው፡፡

፪/ ማንኛውም የህክምና ቦርድ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት መጠንን የሚተምነው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ በሚወጣው ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፡፡

፫/ አስተዳደሩ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በአንድ የህክምና ቦርድ የተሰጠ ውሳኔ በሌላ ህክምና ቦርድ እንደገና እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**33. Assessment of Employment Injury**

1/ The extent of employment injury sustained by an employee shall be assessed by authorized medical board.

2/ any medical board shall assess the extent of employment injury based on the schedule issued pursuant to Article 29 of this Proclamation.

3/ when it deems necessary, the Administration may refer the assessment of a medical board to another medical board for further evaluation.

https://chilot.me



፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀፅ (፫) መሠረት በአንድ የህክምና ቦርድ የተሰጠ ውሳኔ በሌላ ህክምና ቦርድ እንደገና ሲታይ ውጤቱ ከመጀመሪያው የህክምና ቦርድ ውጤት ልዩነት ቢኖር ተቀባይነት የሚኖረው ማስረጃ በአስተዳደሩ ይወሰናል፡፡

**፴፬. <u>የጉዳት አበል</u>**

በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት ከ፲ በመቶ ያላነሰ ሊድን የማይችል ጉዳት ለደረሰበት የግል ድርጅት ሠራተኛ እንደሁኔታዉ የጉዳት ጡረታ አበል ወይም የጉዳት ዳረጎት ይከፈላል፡፡

**፴፭. <u>የጉዳት ጡረታ አበል</u>**

አንድ የግል ድርጅት ሠራተኛ በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት ከ ፲ በመቶ ያላነሰ ሊድን የማይችል ጉዳት ደርሶበት ደመወዝ የሚያስገኝ ማናቸውንም ሥራ መሥራት የማይችል በመሆኑ ከሥራ ሲሰናበት የጉዳት ጡረታ አበል እስከ እድሜ ልኩ ይከፈለዋል፡፡

**፴፮. <u>የጉዳት ጡረታ አበል መጠን</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭ መሠረት የሚከፈለው የጉዳት የጡረታ አበል መጠን የግል ድርጅት ሠራተኛው ጉዳቱ ከደረሰበት ወር በፊት ያገኝ ከነበረው መደበኛ የወር ደመወዝ ፵፯ በመቶ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት አበል ሊከፈለው የሚችል የግል ድርጅት ሠራተኛ በአገልግሎቱ ሊያገኝ የሚችለው አበል በጉዳት ሊያገኝ ከሚችለው የበለጠ ከሆነ የአገልግሎት ጡረታ አበል ይከፈለዋል፡፡

**፴፯. <u>የጉዳት ዳረጎት</u>**

፩/ አንድ የግል ድርጅት ሠራተኛ ከ ፲ በመቶ ያላነሰ ከሥራ የመጣ ጉዳት ደርሶበት ሥራ ለመሥራት የሚችል ከሆነ የጉዳት ዳረጎት ለአንድ ጊዜ ይከፈለዋል፡፡

4/ If a decision made by one medical board in accordance with Sub-Article 3 of this Article is reconsidered by another medical board, the acceptance of the result shall be determined by the Administration.

**34. <u>Incapacity Benefit</u>**

Incapacity pension for life or incapacity gratuity shall be paid, as the case may be, to an employee of private organization who sustains employment injury of not less than 10%.

**35. <u>Incapacity Pension</u>**

An employee who sustains employment injury of not less than 10% and separates from work due to permanent incapacity that prevents him from engaging in any remunerated work shall receive incapacity pension for life.

**36. <u>Amount of Incapacity Pension</u>**

1/ The amount of incapacity pension to be paid in accordance with Article 35 of this Proclamation shall be 47% of his salary which he was receiving during the month prior to the occurrence of the injury.

2/ If the retirement pension to which the employee is entitled is higher than the incapacity pension to be paid pursuant to Sub-Article (1) of this Article, he shall receive the retirement pension.

**37. <u>Incapacity Gratuity</u>**

1/ An employee who sustains employment injury of not less than 10% without loss of capacity to work shall receive incapacity gratuity in the form of lump sum.

፪/ የግል ድርጅት ሠራተኛው አግባብ ባለው ሕግ ወይም ኅብረት ስምምነት መሠረት በአሠሪው የጉዳት ካሣ ወይም የመድን ክፍያ የሚያገኝ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው የጉዳት ዳረጎት አይከፈለውም፡፡

**፴፰. የጉዳት ዳረጎት መጠን**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፯ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የጉዳት ዳረጎት መጠን የግል ድርጅት ሠራተኛው ጉዳት ከደረሰበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው መደበኛ የወር ደመወዙ ፵፯ በመቶ በ፷ ተባዝቶ የሚገኘው ሂሣብ በሠራተኛው ላይ በደረሰው ጉዳት መቶኛ ተባዝቶ ነው፡፡

**ክፍል ስምንት**

**የተተኪዎች ጡረታ አበልና ዳረጎት**

**፴፱. ጠቅላላ**

፩/ ማንኛውም የግል ድርጅት ሠራተኛ፡-

ሀ) የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ወይም የጉዳት ጡረታ አበል በመከፈል ላይ እያለ፤ ወይም

ለ) ቢያንስ ፲ ዓመት አገልግሎ በሥራ ላይ እያለ፤ ወይም

ሐ) በሥራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት፤

ከሞተ ለተተኪዎቹ የጡረታ አበል ይከፈላል፡፡

፪/ ከአሥር ዓመት ያነሰ አገልግሎት ያለው ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ ከሞተ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) (ሀ) እና (ለ) ለተመለከቱት ተተኪዎች ዳረጎት ይከፈላቸዋል፤

2/ If the employee is entitled to compensation for damage in accordance with the appropriate law or collective agreement from the employer or insurance benefit, he shall not receive the incapacity gratuity to be paid pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

**38. Amount of Incapacity Gratuity**

The amount of incapacity gratuity payable in accordance with Sub-Article (1) of Article 37 of this Proclamation shall be equal to 47% of the monthly salary of the employee which he was receiving during the month preceding the occurrence of the injury multiplied by 60 and the percentage of injury sustained.

**PART EIGHT**

**SURVIVORS PENSION AND GRATUITY**

**39. General**

1/ Pension shall be paid to the survivors of an employee who dies:

a) While receiving retirement or invalidity or incapacity pension; or

b) While in service upon completing at least 10 years of service; or

c) due to employment injury.

2/ If an employee who has not completed 10 years of service dies before he separates from the service, his survivors falling under Sub-Article (3)(a) and (b) of this Article shall receive gratuity.

https://chilot.me


፫/ የሟች ተተኪዎች የሚባሉት የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) ሚስት ወይም ባል፤

ለ) ከ፲፰ ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ልጆች ወይም አካል ጉዳተኛ ወይም አዕምሮ ህመምተኛ ልጅ ሲሆን ዕድሜው ከ፳፩ ዓመት በታች የሆነ፤

ሐ) ልጃቸው ከመሞቱ በፊት ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በሟች ድጋፍ ይተዳደሩ የነበሩ ወላጆች፡፡

**፵. <u>የሟች ሚስት ወይም ባል ጡረታ አበል</u>**

፩/ ለሟች ሚስት ወይም ባል የሚከፈለው የጡረታ አበል ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል ፶ በመቶ ይሆናል፤

፪/ የሟች ሚስት ወይም ባል የጡረታ አበል ተወስኖ በመቀበል ላይ እያለች ወይም እያለ ጋብቻ ከፈጸመች ወይም ከፈጸመ፡-

ሀ) ሚስት ዕድሜዋ ከ፵፭ ዓመት በታች ከሆነ፤ ወይም

ለ) ባል እድሜው ከ፶ ዓመት በታች ከሆነ፤ ጋብቻ ከተፈጸመበት ቀን ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ በመከፈል ላይ ያለው የጡረታ አበል ይቋረጣል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት መቋረጥ የሚገባውን የጡረታ አበል የተቀበለች ወይም የተቀበለ የሟች ሚስት ወይም ባል መልሶ የመክፈል ግዴታ አለባት ወይም አለበት፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች በአካል ጉዳተኛ ሚስት ወይም ባል ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

3/ The following shall be considered as survivors:

a) A widow or widower;

b) Children of the deceased who are under the age of 18 years or in case of disabled child or child with mental health problem, under the age of 21 years;

c) Parents who were wholly or mainly supported by the deceased preceding his death.

**40. <u>Widow's or Widower's Pension</u>**

1/ The amount of pension payable to a widow or widower shall be 50 % of the pension to which the deceased was or would have been entitled;

2/ Widow's or widower's pension shall be discontinued from the beginning of the month following remarriage where:

a) the age of widow is less than 45 years; or

b) The age of widower is less than 50 years.

3/ A widow or widower shall return the pension received in violation of Sub-Article (2) of this Article.

4/ The provisions of Sub-Articles (2) and (3) of this Article shall not be applicable to disabled widow or widower.

https://chilot.me



፭/ ለሟች ሚስት ወይም ባል በዚህ አንቀጽ መሠረት ከአንድ በላይ የጡረታ አበል የሚከፈልበት ሁኔታ ሲያጋጥም አንዱና የሚበልጠው ብቻ ይከፈላል፡፡

**፵፩. የሟች ልጅ ጡረታ አበል**

፩/ ለሟች ልጅ የሚከፈለው የጡረታ አበል ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል ፳ በመቶ ይሆናል፡፡

፪/ ሁለቱም ወላጆቹ ለሞቱበት ልጅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የጡረታ አበል ፴ በመቶ ይሆናል፡፡

፫/ የጡረታ አበል የሚከፈላቸው ወይም ሊከፈላቸው ይችሉ የነበሩ ሁለቱም ወላጆቹ የሞቱበት ልጅ ከእያንዳንዳቸው አበል ፳ በመቶ ይከፈለዋል፤ ሆኖም የጡረታ አበሉ ድምር በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት ሊከፈል ከሚችለው ያነሰ አይሆንም፡፡

**፵፪. የወላጅ ጡረታ አበል**

ለሟች ወላጆች ለእያንዳንዳቸው የሚከፈለው የጡረታ አበል ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል ፲፭ በመቶ ይሆናል፡፡ ሆኖም ከወላጆች ሌላ ተተኪ ከሌለ ፳ በመቶ ይሆናል፡፡

**፵፫. የተተኪዎች ዳረጎት**

በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፴፱ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ለተመለከቱት ተተኪዎች የሚከፈለው የዳረጎት መጠን ለሟች በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈለው ይገባ ከነበረው ዳረጎት እንደአግባቡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵(፩) ወይም አንቀፅ ፵፩ በተወሰነው መቶኛ ተባዝቶ ይታሰባል፡፡

5/ Where a widow or widower is entitled to more than one pensions in accordance with the provisions of this Article, the one that is higher shall be paid.

**41. Surviving Child's Pension**

1/ The amount of pension payable to surviving child shall be 20% of the pension to which the deceased was or would have been entitled.

2/ If both parents are dead, the amount of pension payable to surviving child in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be 30%.

3/ If both parents of a child are dead, he shall receive 20% of the pension to which each of the deceased parent was or would have been entitled; provided, however, that the sum of such pensions shall not be less than the amount payable in accordance with Sub-Article (2) of this Article.

**42. Parent's Pension**

The amount of pension payable to each parent shall be 15% of the pension to which the deceased was or would have been entitled. If there are no survivors other than the parents, the pension shall be 20%.

**43. Survivors' Gratuity**

The amount of gratuity payable to the survivors referred to under Article 39 Sub Article (2) of this Proclamation shall be the amount of gratuity to which the deceased would have been entitled and shall be calculated in accordance with the percentage specified in Article 40(1) or Article 41 of this Proclamation, as the case may be.

https://chilot.me


**፵፬. የተተኪዎች አበል ገደብ**

፩/ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፵ እስከ አንቀፅ ፵፫ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ለተተኪዎች የሚከፈለው አበል ድምር ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል ከነበረው አበል ፻ በመቶ /መቶ በመቶ/ ሊበልጥ አይችልም፤ ከተጠቀሰው መጠን በልጦ ከተገኘ ከእያንዳንዱ ተተኪ አበል ላይ ተመጣጣኝ ቅናሽ ይደረጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የተተኪዎች ጡረታ አበል ከተስተካከለ በኋላ የተተኪዎች ብዛት ከቀነሰ የአበሉ መጠን እንደገና ይስተካከላል፡፡

**ክፍል ዘጠኝ**

**አበልን የሚመለከቱ የወል ድንጋጌዎች**

**፵፭. ስለጡረታ አበልና መጠን መሻሻል**

የአስተዳደሩ የስራ አመራር ቦርድ ወቅታዊ የኑሮ ሁኔታንና የጡረታ ፈንዱን የመክፈል አቅም በማገናዘብ እስከ ፫ (ሦሥት)ሰ ዓመት ባለ ጊዜ ውስጥ ዝቅተኛ ወርሃዊ የጡረታ አበል መጠንና የጡረታ አበል ማስተካከያ ያደርጋል፡፡

**፵፮. የጡረታ አበል አከፋፈልና የመክፈያ ጊዜ**

፩/ የጡረታ አበል የሚከፈለው በየወሩ ይሆናል፡፡

፪/ የአገልግሎት ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው የግል ድርጅት ሠራተኛው በዕድሜ ለጡረታ ብቁ ከሆነበት ቀጥሎ ካለው ወር መጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፡፡

**44. Limit of Survivors' Benefits**

1/ The total amount of benefits payable to survivors in accordance with the provisions from Article 40 up to Article 43 of this Proclamation shall not exceed 100% (hundred percent) of the benefit to which the deceased was or would have been entitled. In the case of excess sum, each survivor's share shall be proportionately reduced to adjust until the total comes down to100%.

2/ If the number of survivors is reduced subsequent to adjustment under Sub-Article (1) of this Article, further adjustment of the amount of benefits shall be made accordingly.

**PART NINE**

**GENERAL PROVISIONS RELATING TO BENEFITS**

**45. Adjustment of Pension and Amount**

The Administration's management board, considering the exisisting living conditions and the ability to pay of the pension fund, shall adjust the minimum monthly pension and pension adjustment within 3(Three) years.

**46. Mode and Period of Payment of Pension**

1/ Payment of pension shall be commenced monthly.

2/ Retirement pension shall commence to accrue as of the first day of the month following that in which the employee retires.

https://chilot.me



፫/ የጤና ጉድለት ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው የግል ድርጅት ሠራተኛው በጤና ጉድለት ምክንያት መሥራት የማይችል መሆኑ በሕክምና ቦርድ ከተረጋገጠበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፡፡

፬/ የጉዳት ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው የግል ድርጅት ሠራተኛው በጉዳት ምክንያት መሥራት የማይችል መሆኑ በሕክምና ቦርድ ከተረጋገጠበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፡፡

፭/ የተተኪዎች ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው ባለመብቱ ከሞተበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፡፡

## ፵፯. የዳረጎት አከፋፈልና የመክፈያ ጊዜ

፩/ ማንኛውም ዳረጎት የሚከፈለው በአንድ ጊዜ ነው፡፡

፪/ የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ዳረጎት ተከፋይ የሚሆነው የግል ድርጅት ሠራተኛው ከሥራ ከተሰናበተበት ቀጥሎ ባለው ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ነው፡፡

፫/ የጉዳት ዳረጎት ተከፋይ የሚሆነው የግል ድርጅት ሠራተኛው ላይ ጉዳት ስለመድረሱና መጠኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

## ፵፰. የይርጋ ጊዜ

፩/ ማንኛውም የውዝፍ ጡረታ አበል ወይም የዳረጎት ክፍያ ጥያቄ ከአምስት ዓመት በኋላ በይርጋ ይታገዳል፡፡

፪/ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ መጠቀም ከሚቻልበት ቀጥሎ ካለው ቀን አንስቶ ነው፤

፫/ በሚከተሉት ምክንያቶች የባከነ ጊዜ ለይርጋ አቆጣጠር አይታሰብም፡-

3/ Invalidity pension shall commence to accrue as of the first day of the month following that in which the invalidity of the employee is ascertained by medical board.

4/ Incapacity pension shall commence to accrue as of the first day of the month following that in which the permanent total incapacity sustained by the employee is ascertained by medical board.

5/ Survivor's pension shall commence to accrue as of the first day of the month following that in which the beneficiary dies.

## 47. Mode and Period of Payment of Gratuity

1/ Payment of any gratuity shall be commenced in lump sum at once.

2/ Retirement or invalidity gratuity shall be payable beginning with the first day of the month following that in which the employee separates from the service.

3/ Incapacity gratuity shall be payable beginning with the day where evidence ascertaining the injury and its degree is submitted.

## 48. Period of Limitation

1/ any claim for payment of arrears of pension benefit or payment of gratuity shall be barred by limitation after five years.

2/ the period of limitation shall begin to run from the day following that in which the right may be exercised;

3/ The period of limitation shall not include the following:

https://chilot.me


ሀ) ባለመብትነትን ለማረጋገጥ የተጀመረ የፍርድ ቤት ሥርዓት እስከሚጠናቀቅ የወሰደው ጊዜ፤

ለ) ማንኛውም የግል ድርጅት ለሠራተኛው የጡረታ አበል ውሳኔ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን እንዲያሟላ በአስተዳደሩ በጽሁፍ ተጠይቆ የሠራተኛውን ማስረጃ አሟልቶ ባለመላኩ ያለፈው ጊዜ፤

ሐ) አስተዳደሩ የቀረበለትን የክፍያ ጥያቄ መርምሮ ለመወሰን የወሰደው ጊዜ፡፡

**፵፱. የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ስላለመደረጉ**

የግል ድርጅት ሠራተኛው አገልግሎት በማንኛውም ምክንያት ቢቋረጥ ለግል ድርጅቱም ሆነ ለግል ድርጅት ሠራተኛው የጡረታ መዋጮ ተመላሽ አይደረግም፡፡

**፶. አበል የማግኘት መብትን ማስተላለፍ ስላለመቻሉ**

አበል የማግኘት መብት የዕዳ መያዣ ሊደረግ ወይም በውርስም ሆነ በሌላ በማናቸውም መንገድ ሊተላለፍ አይችልም፡፡

**፶፩. ስለአበል በሕግ መከበር**

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ አበል፡-

፩/ ለመንግሥት ገቢ የሚሆን መቀጮ፣ ግብር ወይም ቀረጥ ለመክፈል፤ ወይም

፪/ አግባብ ባለዉ ሕግ መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታን ለመወጣት፤በፍርድ ቤት ካልታዘዘ በስተቀር፤

በሌላ ዕዳ ምክንያት አይከበርም፡፡

a) period lapsed due to a court process started to establish right;

b) After written request of the administration, period lapsed due to failure of a private organization to submit relevant evidentiary documents of pension benefit entitlement for its employee;

c) Periods necessary for the decision of benefit entitlement by the administration.

**49. Non-Reimbursement of Pension Contribution**

If the employment contract of an employee is terminated due to any reason, the pension contribution may not be reimbursed for the private organization as well as for the employee.

**50. None-Transferability of Benefit Entitlement**

The right to receive benefits shall not be pledged or transferred by inheritance or any other means.

**51. Attachment of Benefits**

Benefits payable in accordance with this Proclamation shall not be attached in relation to any debts unless ordered by a court in respect of:

1/ public fines, taxes or charges; or

2/ fulfillment of obligation to supply maintenance in ordered by the court accordance with the relevant law.

https://chilot.me


፫/ የማሕበራዊ ጤና መድህን አዋጅ ቁጥር ፮፻፺/፪ሺ፪ አንቀጽ ፱ እና የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ለማሕበራዊ ጤና መድህን የሚሠበሠብ የጤና መድህን መዋጮ በየወሩ ከጡረታ አበል ላይ ተቀንሶ ለጤና መድህን ፈንድ ገቢ ይደረጋል፤ ሆኖም፡-

ሀ) ወርሃዊ የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት በሠራተኛነት በመቀጠር ደመወዝ የሚያገኝ ከሆነ የጤና መድህን መዋጮ የሚቀነሠው በየወሩ ከሚከፈለው ደመወዝ ላይ ብቻ ይሆናል፤

ለ) ዋና ባለመብት በመሆን ጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት የተተኪም የጡረታ አበል የሚያገኝ ከሆነ የጤና መድህን መዋጮ የሚቀነሠው ዋና ባለመብት በመሆን ከሚያገኘው የጡረታ አበል ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

## ክፍል አሥር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፶፪/ የመብቶች ግንኙነት

፩/ በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት በዚህ አዋጅ በሚሸፈን የግል ድርጅት ከተቀጠረና ለጡረታ መውጫ ዕድሜ ያልደረሰ ከሆነ አዲሱ አገልግሎት ከቀድሞ አገልግሎቱ ጋር ተደምሮ ይታሰብለታል፡፡ ሆኖም እንደገና የታሰበው አበል ከቀድሞው አበል ያነሰ ከሆነ የቀድሞውን አበል የማግኘት መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ስራ በመመለስ ለፈጸመው አገልግሎት የሚከፈለው አበል ወይም የጡረታ መዋጮ አይኖርም፡፡

3/ Notwithstanding the provision of Article 9 of Social Health Insurance Proclamation No. 690/2010 and Sub-Article (1) and (2) of this Article, a contribution for social health insurance shall be deducted monthly from pension benefit and transferred to social health insurance fund. However:

a) If the beneficiary who receives monthly pension benefit also receives salary from employment, a contribution for social health insurance shall be deducted only from his monthly salary;

b) If the principal beneficiary who receives pension benefit also receives survivors' pension benefit, the contribution for social health insurance shall be deducted only from the pension benefit of principal beneficiary.

## PART TEN

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 52. Relationship between Entitlements

1/ An employee who receives pension benefit from private organization pension schema if employed in a private organization covered by this Proclamation and has not reached the retirement age, his new service shall be added to his previous service; provided, however, that if the retirement benefit based on the accumulated service is less than the previous one, without prejudice to his right to receive the previous pension, he may not receive any payment or contribution reimbursement for the new service he provided.

https://chilot.me



፪/ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ የግል ድርጅት ውስጥ በመቀጠር በሁለት ወይም ከዚያ በላይ የግል ድርጅት ደመወዝ ከሚከፈለው ሠራተኛ የጡረታ መዋጮ የሚሠበሠበው ሠራተኛው ከመረጠውና በአንድ የግል ድርጅት ከሚከፈለው ደመወዝ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡ሆኖም የግል ድርጅት ሠራተኛው የመንግሥት ሠራተኛም ጭምር ከሆነ በግል ድርጅቱ ከሚከፈለው ደመወዝ ላይ የጡረታ መዋጮ አይሠበሠብም፣ አገልግሎቱም ለጡረታ አበል አወሳሰን አይታሰብም፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ ወይም በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት መጦሪያ ዕድሜ ፷ ላይ ከመድረሱ አስቀድሞ የጡረታ አበል የተወሠነለት ባለመብት በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት እንደገና በመቀጠር የፈጸመው አገልግሎት ከቀድሞ አገልግሎቱ ጋር ተዳምሮ አበሉ ተሻሽሎ የሚከፈለው መጦሪያ ዕድሜ ፷ ላይ ሲደርስ ብቻ ይሆናል፡፡ሆኖም በስራ ላይ ጉዳት ወይም በጤና ጉድለት ምክንያት ሠራተኛው ደመወዝ የሚያስገኝ ማናቸውንም ስራ መስራት የማይችል መሆኑ በህክምና ቦርድ ተረጋግጦ ከስራ ሲሠናበት ከስራ ከተሠናበተበት ወር ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ አበሉ ተሻሽሎ ይከፈላል፡፡

**፶፫. <u>መረጃ የመስጠትና የመተባበር ግዴታ</u>**

፩/ ማንኛውም የግል ድርጅት ከአስተዳደሩ በሚተላለፈው መመሪያ መሠረት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ እያንዳንዱን የግል ድርጅት ሠራተኛ የሚመለከቱ መረጃዎችና ማስረጃዎች ማሰባሰብ፣ ማጠናቀር፣ ማደራጀትና በአስተዳዳሩ በሚወሰነው ጊዜና ቅጽ መሠረት

2/ if a private organization employee is employed and salaried from two or more private organizations, the pension contribution may be collected according to his choice from salary paid by one private organization; provided, however, that if a private organization employee is a public servant as well, the pension contribution may not be collected from a salary paid by any private organization, and the service may not be calculated for pension benefit.

3/ If a re-employed beneficiary was entitled to a retirement pension benefit pursuant to this Proclamation or Public Servant Pension Proclamation before the retirement age of 60, the new service that has been rendered by him shall be added to his pension benefit with the pervious service in accordance with Sub-Article (1) of this Article only when he attains the retirement age of 60; provided, however, that if it is ascertained by a medical board that the employee of a private organization is incapable of fulfilling service due to employment injury or health problems and separated from service, his pension shall be re-considered starting from the next month following his separation from service.

**53. <u>Obligation to Provide Evidentiary Data and Duty to Cooperate</u>**

1/ In accordance with the direction of the Administration any private organization shall collect, compile and submit to the administration, in accordance with the form and within the time limit specified by the Administration, particulars and

https://chilot.me


ለአስተዳደሩ የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል ማንኛውም ሰው የጽሑፍ ማስረጃ እንዲልክ ወይም ቀርቦ አስተያየትና መረጃ እንዲሰጥ በአስተዳደሩ ሲጠየቅ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፫/ የሚመለከታቸው አካላት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፮) በሚሰጥ ውክልና መሠረት የጡረታ መዋጮ በመሰብሰብ ረገድ ከአስተዳደሩ ጋር የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

**፶፬. <u>የአስተዳደሩ ውሣኔዎች</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚሰጥ ለማናቸውም ዓይነት አበል ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መሟላታቸው የሚረጋገጠውና የአበሉ ዓይነትና መጠን የሚወሰነው በአስተዳደሩ ይሆናል፡፡

፪/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ውሣኔ የሚሰጠው የራሱን የመረጃ ማህደር፣በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ እና ፶፫ መሠረት የሚተላለፉትን መረጃዎች እና እንደ አግባቡ ባለመብቱ የሚያቀርባቸውን ተጨማሪ ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ይሆናል፤

፫/ በአስተዳደሩ የመረጃ ማህደርና በሌላ አካል በቀረበለት ማስረጃ መካከል ልዩነት ቢፈጠር ተቀባይነት የሚኖረው ማስረጃ በአስተዳደሩ ይወሰናል፡፡

evidences relating to each of its employees which are necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ Any person shall furnish written evidence or appear and testify or give his opinion when so requested by the Administration for the purpose of implementing this Proclamation.

3/ Appropriate bodies shall have the duty to cooperate with the Administration in collecting pension contributions pursuant to delegations of powers under Sub-Srticle (6) of Article 12 of this Proclamation.

**54. <u>Decision of the Administration</u>**

1/ The fulfillment of conditions for entitlement to any kind of benefit payable in accordance with this Proclamation and the amount of the benefit shall be decided by the Administration.

2/ The decision of the Administration to be rendered in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be based on its own record, evidentiary data submitted to it in accordance with Article 16 and 53 of this Proclamation, and as may be appropriate, on additional evidences produced by the beneficiary.

3/ In the case of a difference between the records of the Administration and evidentiary data submitted to it, the prevailing evidence shall be decided by the Administration.

https://chilot.me



**፶፭. ውሣኔን እንደገና ስለመመርመር**

፩/ ቅሬታ ያለው ባለመብት በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም በራሱ አነሳሽነት አስተዳደሩ ቀደም ብሎ የሰጠውን ውሳኔ እንደገና ለመመርመር ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ የተደነገገው ቢኖርም አስተዳደሩ ውሣኔውን እንደገና ሲመረምር የአበል መሠረዝ፣ መቀነስ ወይም መቋረጥ ሊያስከትል የሚችል በቂ ምክንያት ያገኘ እንደሆነ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ሊሰረዝ፣ ሊቀነስ ወይም ሊቋረጥ በሚገባው አበል መጠን ክፍያው ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ የተደነገገው ቢኖርም እንደገና በተደረገው ምርመራ የጡረታ አበል እንዲቀነስ አስተዳደሩ ከወሰነ ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌ ውጪ ያለአግባብ የጡረታ አበል ከተከፈለ አስተዳደሩ ከባለመብቱ አበል ላይ እየቀነሰ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

**፶፮. ስለይግባኝ**

፩/ አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፬ ወይም አንቀፅ ፶፭ መሠረት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ባለመብት በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፯/፪ሺ፲፬ ለተቋቋመው የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይግባኝ የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

፪/ የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፯/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፶፮ ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት በግል ድርጅት ሠራተኞች የሚቀርቡ ይግባኞችን በሚመለከትም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**55. Review of Decisions**

1/ The Administration may review its previous decision upon request by an aggrieved beneficiary or on its own initiative.

2/ Without prejudice to the provision of Article 51 of this Proclamation, where upon review, the Administration finds that there is reasonable ground for cancellation, deduction or termination of benefits, it may suspend payment to the extent the benefit is to be cancelled, deducted or terminated.

3/ Notwithstanding the provisions of Article 51 of this Proclamation, if the Administration, upon review, has decided to deduct the benefit or the benefit paid is contrary to this Proclamation, it shall have the power to deduct the amount paid thereof from the benefit of the beneficiary and transfer same to the Pension Fund.

**56. Appeal**

1/ A beneficiary who is aggrieved by the decision of the Administration made pursuant to Article 54 or Article 55 of this Proclamation shall have the right to lodge an appeal to the Social Security Appeal Tribunal established by Public Servant Pension Proclamation No 1267/2022.

2/ Article 56 of the Public Servants Pension Proclamation No1267/2022 shall be applicable to employees of private organizations lodging appeals pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

https://chilot.me



**፶፯. ከግብር ነፃ ስለመሆን**

በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚከፈል የጡረታ አበል፣ ከሚሰበሰብ የጡረታ መዋጮ እና ከጡረታ ፈንድ ኢንቨስትመንት ከሚገኝ ትርፍ ላይ ግብር አይከፈልም፡፡

**፶፰. የመረጃ አያያዝ ሃላፊነት**

አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚመዘግባቸውን መረጃዎች የመሰብሰብና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አደራጅቶ የመያዝ ሃላፊነት አለበት፡፡

**፶፱. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

፩/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ለተፈጠሩ ሕጋዊ ሁኔታዎች ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩ ሕጎችና መመሪያዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

፪/ አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ የተጠቀሰውን የአካል ጉዳት መወሰኛ ሠንጠረዥ እስከሚያወጣ ድረስ የህክምና ቦርዶች የሚከተሉት አሠራር ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

**፷. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፤

፪/ አስተዳደሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፷፩. ቅጣት**

የያዘውን ማስረጃ በዚህ አዋጅ መሠረት ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም የዚህን አዋጅ ድንጋጌ አፈጻጸም የሚያሰናክል ተግባር የፈጸመ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል፡፡

**57. Tax Exemption**

No tax shall be payable on benefits received, pension contribution collected and profits earned from investment of the Pension Fund, in accordance with this Proclamation.

**58. Responsibility of data keeping**

The Administration shall be responsible for the collection and digitization of data registration in accordance with this Proclamation.

**59. Transitory Provisions**

1/ Previous laws and Directives shall remain applicable to legal situations created before the coming into force of this Proclamation.

2/ Until the Administration issues the schedule referred to in Article 29 of this Proclamation to determine the degrees of incapacity, the practices followed by medical boards shall remain applicable.

**60. Power to Issue Regulation and Directive**

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Administration may issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulations issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

**61. Penalty**

Whosoever is unwilling to submit evidentiary document under his possession or obstructs the implementation of this Proclamation is punishable by the relevant provision of Criminal Law.

https://chilot.me


**፷፪. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>**

የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፭/፪ሺ፫ እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፰/፪ሺ፯ ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል፡፡

**፷፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፱ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**62. <u>Repealed laws</u>**

Private Organization Employees' Pension Proclamation No 715/2011 and Amendment Proclamation No. 908/2015 here by repealed and replaced by this Proclamation.

**63. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, on this 18th Day of March, 2022**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://chilot.me

https://chilot.me